SCHWEIZERISCHE FLÜCHTLINGSHILFE
ORGANISATION SUISSE D'AIDE AUX RÉFUGIÉS
ORGANIZZAZIONE SVIZZERA AIUTO AI RIFUGIATI
www.osar.ch

# ባይሮፕላን ማረፊያ የጥገኝነት ማመልከቻ ለሚያቀርቡ የሚሆን ኣስፈላጊ ማስረጃ

ከኣገርዎ ተሰድደው በስዊዘርላንድ የጥገኝነት ማመልከቻ በማቅረብ ላይ ነው ያሉት? በስዊዘርላንድ የስደተኞች ረዳት ድርጅት (SFH) ይህንን የማስረጃ ጽሑፍ ኣዘጋጅቷል። ይህ ጽሑፍ ባይሮፕላን ማረፊያ የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት ዋና ዋና ቀደም ተከተሎችን ያብራራል።

ይህ የስዊዘርላንድ የስደተኛች ረዳት ድርጅት (SFH) ራሱን የቻለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የስደተኞችና ጥገኝነት ለሚጠይቁ መብታቸውን ለማስከበር የሚታገል ድርጅት ነው። ዌብ ሳይታችን www.osar.ch ሲሆን ባለጉዳዮች በተለያዩ ቋንቋዎች ተጨማሪ ማስረጃ በ www.for-refugees.ch ማግኘት ይችላሉ።

## 1. የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ

### 1.1 ባይሮፕላን ማረፊያ ጥገኝነት ማመልከት

የጥገኝነት ማመልከቻውን ባንድ የስዊዘርላንድ ኣይሮፕላን ማረፊያ ኣቅርበዋል።

→ ጉዳይዎን በሚጣራበት ግዜ (ምናልባትም ለጊዜው) ባይሮፕላን ማረፊያው ትራንዚት ባለበት ቅጥር ግቢው ዉስጥ ይኖራሉ።
**እወቁት**፡ ዉሳኔዉን በመቃወም ይግባኝ ማለት ይችላሉ።
→ ፓስፖርትዎና ሌላ መታወቅያ ወረቀቶች ያስረክባሉ ለጥያቄም ይቀርባሉ።
→ የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ ይመዘገቡና ፎቶ ይነሳሉ ከዛም የጣቶችዎ ኣሻራ ይወሰዳል። የስዊዘርላንድ ባለስልጣናት የርስዎ ኣሻራ በማእከላይ የዳታ ባንክ (Eurodac) ውስጥ፣ ባንድ የኤውሮጳ ማሕበር ኣገር፣ በኖርዌይ ወይም በኣይስላንድ የተመዘገበ እንደሆን ይመረምራሉ። እንድዛ ከሆነና፣ እርስዎ በስዊዘርላንድ ውስጥ ባለቤትም ይሁን ልጆች የሌለዎት ከሆነ፣ የርስዎን ጉዳይ ለማጣራት ይሄ ኣገር ነው ሓላፊነት ያለው። ስዊዘርላንድም እርስዎን ሓላፊነት ወዳለበት ኣገር ሊመልስዎት ይሞክራል። ባንድ የኤውሮጳ ኣገር፣ ኣንድ ጊዜ ብቻ ነው ጥገኝነት ማመልከት የሚችሉት (የዳብሊን-ስምምነት)(DUBLIN-Verfahren)። የመጀመርያው ኣገር ብቻ ነው፣ የርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ በትክክል መቀበልና መመረምር ያለበት። ከዚህ በፊት በሌላ የኤውሮጳ ኣገር ጥገኝነት ያመለከቱ ከሆነና፣ ይህ የኤውሮጳ ኣገር የጥገኝነት ማመልከቻየን በትክክል ኣላጣራልኝም የሚሉ ከሆነ፣ ባይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ወደሚገኘው የሕግ ማማከርያ ጽሕፈት ቤት (Rechtsberatungsstelle) መሄድ ኣለብዎት። ስዊዘርላንድ ከሚልክዎት ኣገር ለምሳሌ፤ ለስደተኛነት ብቁ እያለሁ፣ ያ ኣገር የጥገኛነት ማመልከቻየን በደንብ ሳያጠና በቀጥታ ወደ ትውልድ ኣገሬ ይልከኛል፣ የሚል ፍርሃት ካለብዎት፣ ስዊዘርላንድ ውስጥ ለመቅረት ይጠይቁ። ስዊዘርላንድ ሊልክዎት ከፈለገው ሌላ የኤውሮጳ ኣገር ለምሳሌ በቀጥታ ወደ ግርፋት፣ ኢሰብኣዊ ወይም የሚያዋርድ ቅጣት ወይም ግፍ ወደሚደርስብዎ ትውልድ ኣገርዎ የመላክ ፍርሃት ያለብዎት ከሆነም፣ ስዊዘርላንድ ውስጥ ለመቅረት ይጠይቁ።

## 1.2 ምዝገባ

የሚመለካታቸው መስርያ ቤቶቹ ስለ እራስዎና ስለ ቤተሰብዎ ማንነት፣ እንዲሁም እንዴት ወደ ስዊዘርላንድ እንደመጡ፣ የስደትዎን ምክንያት ይጠይቃሉ። ቃለ መጠይቅ በምያደርጉበት ጊዜ ኣንድ የመንግስት ሰራተኛ ወንድ ወይም ሴት ኣስፈላጊ ከሆነ ኣንድ ወይም ኣንዲት ኣስተርጓሚ ይኖራል።

→ ኣገርዎን ለቀው እንዲወጡ ያስገደድዎትን ዋና ዋና ምክንያቶች ሁሉ ይዘርዝሩ።
→ ካጋጠምዎት ችግሮች ውስጥ ወንድ ወይም ሴት ፊት ሊናገሩዋቸው የማይፈልጉ ነገሮች ካሉ ንገሩ።
→ የመታወቅያ ወረቀት ማስረከብ የማይችሉ ከሆኑ ምክንያቱን ይግለጹ።
→ የሆነ ያልተረዱት ነገር ካለ መናገር ኣለብዎት።

ቃለ መጠይቁን ሲጨርሱ የሆነ ፕሮቶኮል (ቃለ  ጉባኤ) መፈረም ኣለብዎት። የዚሁን ፕሮቶኮል ትክክለኛነቱንና ሙሉ በሙሉ መጻፉን ማረጋገጥ ኣለብዎት።






## 1.3 ሰነዶች/ የመረጋገጫ ሰነድ

→ ላጋጠምዎት ችግሮች ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ሰንዶች በመዝገብ እንዲያዝ ኣስረክቡ።

→ ከሚያስረክቡት ሰነዶችም ለርስዎ ቅጂ (ኮፒ) መያዝ ኣለብዎት፨

## 1.4 መግለጫ

ምናልባት የርስዎን ጉድይ ለማጣራት ተጨማሪ መግለጫ ይደረጋል።

→ የመጣሁበት ኣገር ነው ብለው በሰጡት ኣገር ጥርጣሬ ካለ በኣንድ የቋንቋ ኣዋቂ ሊጠየቁ ይችላሉ፡ እንዲሁም ስለ ኣገርዎ ያልዎትን እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ሊመረመሩ ይችላሉ።
→ በሰጡት እድሜ ጥርጣሬ ካደረ የእድሜዎ ግምጋሜ ምርመራ ሊደረግ ይችላል።

## 1.5 የሚቀጥለውስ እርምጃ?

ባይሮፐላን ማረፊያው ውስጥ፣ ባንድ የፌደራል ኢሚግሬሽን ጽሕፈት ቤት ባለስልጣን፣ ጥገኝነት ለሚያመለክትበት ምክንያት ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ ያደርጉና እንደሚቀጥሉት ይሰጥዎታል፤

- ያቀረቡት ምክንያት ኣልታመነም። ይህን ተቃዉመው ይግባኝ ማለት ይችላሉ።
- ኣሉታዊ የጥገኝነት ዉሳኔ። ይህን ተቃዉመው ይግባኝ ማለት ይችላሉ።
- ወደ ስዊዘርላንድ ውስጥ እንዲገቡ ይፈቀድና እዛ የጥገኝነት ማመልከቻዎ እንዲጣራ። እንደዚህ ዓይነት ፈቃድ ግን ለጥቂት ጉዳዮች ነው የሚሰጠው።

→ ኤን (N) መታወቅያ ወረቀት ይሰጥዎታል (ጥገኝነት ለሚጠይቁ የሚሰጥ መታወቅያ ወረቀት)

  

# 2 ቃለ መጠይቕ

የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ የሚያደርጉት ቃለ መጠይቅ በጣም ኣስፈላጊ ነው። ኣንድ ጊዜ ወይም በተዳጋጋሚ ሊጠየቁ ይችላሉ። መስርያ ቤቶቹ እርስዎ ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ማለት በዛው ባደረጉት ቃለ መጠይቅና በተጻፈው ቃለ ጉባኤ (ፕሮቶኮል) መሰረት ኣድረገው ይወስናሉ።

## 2.1 በሚደረገው ቃለ መጠይቅ ማን ተካፋይ ይሆናል?

→ ቃለ መጠይቁን የሚመራ ወይም የምትመራ ኣንድ የመንግስት ስራተኛ ይኖራል።
→ ኣንድ ኣስተርጓሚ ወይም ኣስተርጓሚት የሚተረጎመውን ሁሉ ያስተረጉማል የተሰጠው መግለጫ ላይ ግን ፍርድ ወይም ኣጠቃላይ መግለጫ ማውደቅ ኣይፈቀድም። ግለ ሰቡ ማንነቱ እንዳይጠቀስ ማድረግ ይቻላል። ኣንድ ራስዎ የመረጡት ኣስተርጓሚ ይዘው መምጣት ይችላሉ፣ ግን ይህ ኣስተርጓሚ ራሱ ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ የሚገኝ መሆን የለበትም።
→ ኣንድ የእርዳታ ድርጅት ወኪል (ኣንድ የመንግስታዊ ድርጅት ኣባል ያልሆነ) የርስዎን ጉዳይ ይታዘባል። ይህ ሰው ተጨማሪ ጥያቄዎች እንዲቀርብ እንዲሁም የቃለ መጠይቁ ሪፖርት ለድርጅቱ እንዲተላለፍ ሊያደርግ ይችላል።
→ እንዲሁም ራስዎን የውክሉት የሕግ ወኪል (ጠበቃ) ወይም ሌላ ለእድሜ የደረሰ ሰው (ግን ራሱ የጥገኝነት ማመልከቻ በማቅረብ ላይ የሚገኝና መልስ ያላገኘ) ሊሸኝዎት ይችላል።

## 2.2 የሚጠየቁት ጥያቄዎች

እንደተለመደው ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት መንገድ (ዘዴ) እንደሚከተለው ነው፡

ከትውውቅ በኃላ ቃለ መጠይቁ በእንዴት ኣኳሃን እንደሚካሄድና የርስዎ መብትና ግዴታ ይገለጽልዎታል። ከዛ የመንግስቱ ባለ ስልጣን (ሃላፊው) **ስለ ሁኔታዎ የሚመለከቱትን ጥያቄዎች** ያቀርባል ወይም ታቀርባለችባ። ይህን ማለት ስለ፡
→ ማንነትዎና የርስዎን ማንነት የሚያረጋግጡ ሰንዶች
→ የርስዎ ቤተሰብና ዘመዶች
→ የወታደራዊ ኣግልግሎት
→ ካኣገርዎ ወደ ስዊዘርላንድ በየትኛው መንገድና እንዴት እንደመጡ
→ በኣገርዎና በስዊዘርላንድ የሰሩት ስራ
→ ሌላ ውጭ ኣገር የኖሩበት ቦታ ካለ
→ የሕግ ወኪል በኣገርዎ ወይም በስዊዘርላንድ

በመጨረሻ በምን ምክንያት በስዊዘርላንድ ጥገኝነት እንደጠየቁ ለመግለጽ እድል ይሰጥዎታል።

**በሕጉ መሰረት (ዓንቀጽ 3 የጥገኝነት ሕግ) ስደተኞች ጥገኝነት (ኣሳይለም) ይሰጣቸዋል።**

*ስደተኞች ሲባል ከኣገራቸው መንግስት ጋር ወይም በመጨረሻ ጊዜ የሚኖሩበት የነበረ ኣገር በዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የኣንድ የተውሰነ ማኅበራዊ ወገን ኣባል በመሆን ወይም ባልዎት የፖለቲካ ኣስተያየት ምክንያት ከፍተኛ ኪሳራ ሲደርስባቸው ወይም ከፍተኛ ኪሳራ ይደርስብኛል ብለው ፍርሃት ካላቸውና ለዚሁም የሚያስተማምን ምክንያት ካቀረቡ። ከፍተኛ ኪሳራ ሊባል የሚችለው በራስዎን፣ በህይወትዎን ወይም ብነጻነትዎ ከባድ ችግር ካጋጠምዎት እንዲሁም የኣእምሮ ጭንቀት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ካጋጠሙ ነው።*

*ለሴቶች የሚያጋጥም ለየት ያለ ችግር ኣትኩሮ ይደረግበታል።*

## 2.3 በስዊዘርላንድ የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ

ቃለ መጠይቕ በሚያደርጉበት ጊዜ ኣገርዎን ለቀው እንደሰደዱ ያደረግዎት ዋና ምክንያት ሁሉ እና ለምን በስዊዘርላንድ ጥገኝነት ማግኘት እንደሚፈልጉ መግለጽ ኣለብዎት። ያለ ፍራሃት ነጻ ሆነው መናገር ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ ተሳታፊ የሚሆኑት ሰዎች የሚስጢር መገደብ ግዴታ ኣለባቸው እንዲሁም እርስዎ የሚገልጹት ሁኔታ ለማንም ሰው እንዲነገር ኣይፈቀድም።

ይህ የቃለ መጠይቁ ክፍል በጣም ኣስፈላጊ ነው። ኣገርዎን ለቀው እንዲወጡ ያስገደድዎት በምን ምክንያት እንደሆነ ወይም ማን እንደሆነ እንዲገልጹ ይጠየቃሉ።

→ የሚሰጡትን መልስ በእውነት የተሞረከሰ መሆን ኣለበት ። በተቻልዎት መጠን በዝርዝር ይግለጹ።
→ የሚሰማዎትን ስሜት ሁሉ ይግለጹ፣ ካጋጠምዎት ችግሮች ውስጥ ወንድ ወይም ሴት ፊት ሊናገሩዋቸው የማይፈልጉ ነገሮች ካሉ ንገሩ።
→ በኣገርዎ ያጋጠምዎት የፖለቲካ ችግርን የሚመለከቱ ሰነዶች ይዘው ይምጡ። (የፖሊስ የእድሜ ወረቐት፣ የእስር ቤት ሰነዶች፣ የማስፈራራት ደብዳቤዎች፣ የሓኪም የምስክር ወረቀት፣ ጋዜጣዎች፣ ፎቶ ወዘተ። ቅጂ ደግሞ ለእርስዎ መያዝ ኣለብዎት)።
→ ከዚህ በፊት ሌላ የኤውሮጳ ኣገር ውስጥ ነበሩ፣ ይሄ ኣገርስ በቀጥታ ወደ ግርፋት፣ ኢሰብኣዊ ወይም የሚያዋርድ ቅጣት ወይም ግፍ ወደሚደርስብዎ ትውልድ ኣገርዎ እንዳይመልስዎት ይፈራሉ፤ ይሄንን ይናገሩ። ስላለብዎት ፍርሃት ኣስፍተው ይግለጹ።

ምናልባት ያልተጣራ ነገር ካለ፣ ኣለመረዳዳት እንዲሁም የተምታታ ነገር ካለ ተጨማሪ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ። የሚሰጡት መልስ ሁሉ በጽሁፍ መስፈር ኣለበት ለእርስዎም እንዲተረጎምልዎት ይደረጋል።

## 2.4 ለቤተሰብ የሚደረገው ቃለ መጠይቅ

የቤተሰብ ኣባላት ሁሉ ኣብረው ይጠየቃሉ። ኣንድ ለእድሜ የደረሰ የቤት ሰቡ ኣባል በሚጠየቅበት ጊዜ ሌሎቹ ሌላ ክፍል ውስጥ ይቆያሉ። ልጆችም ሌላ ተቃዋሚ ነገር ከሌለ ከቤተሰባቸው ፊት ይጠየቃሉ ።




## 3 ቃለ ጉባኤ (ፕሮቶኮል)

የተደረገው ቃለ-መጠይቅ ሁሉ በፕሮቶኮል ፎርም ይጻፋል። ቃለ-መጠይቁን ካደረጉ በኃላ ፕሮቶኮሉ ይተረጎምለዎታል። ገጹ በግጽ ኢንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

→ ያልተረዱት ነገር ቢኖር መንገር ኣለብዎት። የተጻፈውን ፕሮቶኮል ደግሞ ልክ እንዳሉት የተጻፈ መሆኑን ያረጋግጡ። ያልተጣራ ነገር ካለ ወይም ስህተት ካለ መታረም ኢንዳለበት ይንገሩ።

ከቃለ መጠይቁ በኃላ ያልነገሩት ለስደትዎ ምክንያት ካለ ይጠየቃሉ። ሊገልጹት የሚፈልጉት ምክንያት እንደገልጹና የተጻፈውን ፕሮቶኮል ደግሞ እውነት መሆኑን በፊርማዎ ያረጋግጣሉ።

## 4 የጥገኝነት ውሳኔ መስጠት

ኣንዳንድ ጊዜ ባይሮፕላን ማረፊያ ለሚቀርቡ የጥገኝነት ማመልከቻ ማጣራቱ **ጥቂት ቀናት ወይም ሳምንቶች** ብቻ ነው የሚፈጀው። የስደተኞች ጽሕፈት ቤት በሃያ ቀናት ውስጥ የመጀመርያዉን ዉሳኒ ካልወሰነ፣ ወዳንድ ካንቶን ሊገቡ ይችላሉ። ባይሮፕላን ማረፊያው ቢበዛ ለስድሳ ቀናት ሊቆዩ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ባይሮፕላን ማረፊያው ከሚገኘው ማማከርያ መስሪያ ቤት ጋር በጊዜው ይገናኙ። (የኣድራሻዎች ዝርዝር Adressliste: http://www.fluechtlingshilfe.ch/hilfe/nuetzliche-adressen)!

እንደተለመደው የውጭ ኣገር ስደተኖች ጉዳይ ኣጣሪ መስርያ ቤት በጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ ወይም ደግሞ በጣልያንኛ ቋንቋ በጽሑፍ መልክ ይላክልዎታል።

ባይሮፕላን ማረፊያው የሚደረገው ማጣሪያ የሚቀጥሉትን ዉሳኔዎች ያጠቃልላል።

### 4.1 ወደ ስዊዘርላንድ የመግባት ፈቃድ

የፌደራል ጽሕፈት ቤቱ ወደ ስዊዘርላንድ ውስጥ እንዲገቡና እዛ የጥገኝነት ማመልከቻዎ እንዲጣራ ወስኗል። ይህ ማለት ግን የጥገኝነት ጥያቄዎ ተወስኗል ማለት ሳይሆን ወደ ስዊዘርላንድ የመግባት ፈቃድ ብቻ ማለት ነው።

### 4.2 ጊዚያዊ ተቀባይነት

ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ተቀባይነት ባያገኙም ኤፍ(F) የመኖርያ ፈቃድ ኣውጥተው በስዊዘርላንድ መኖር ይችላሉ። እህ ሁኔታ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ደግሞ ወደ ኣገርዎ ለመመለስ የማይቻል ከሆነ ወይም ወደ ኣገርዎን ለመመለስ የማይገፋፋ ካባድ ኣደጋ ሲኖር ነው። ለምሳሌ የእርስ በርስ ጦርነት ካለ ወይም ደግሞ ካባድ ህመም ሲያጋጥም ነው።

 

## 4.3 ኣሉታዊ ውሳኔ

***በቂ ምኽንያት ያለው ኣሉታዊ ውሳኔና ወደ ኣገርዎ እንዲባረሩ የሚደረግ የጥገኝነት ማመልከቻ ውሳነ***

*ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ተቀባይነት ኣላገኘም እና ስዊዘርላንድን ለቀው መውጣት ኣለብዎት። እንደ ደንቡ እስከሚመለሱ ድረስ ካይሮፕላን ማረፊያውን ቅጽር ግቢ መውጣት ኣይችሉም። እንደዚህ ኣይነት ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችለው ያቀረቡት የስደት ምክንያት በመስርያ ቤቱ ኣስተያየት በቂ ኣይደለም የሚል ግምት ካለ ወይም ያቀረቡት የርስዎ ታሪክ በማይታመን ሁኔታ ከገለጹት ወይም ደግሞ ማረጋግጫ ሳያቀርቡ ሲቀሩ ነው።*

***ያለ በቂ ምኽንያት የተወሰነ ኣሉታዊ የጥገኝነት ውሳነ (ግምት ውስጥ የማይቀርብ ውሳኔና ወደ ሶስተኛ ኣገር ማባረር ወይም ወደ ኣንድ የኤውሮጳ ኣገር፣ ኖርዌይ ወይም ኣይስላንድ ማባረር)***

*የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ ወድያው ቃለ መጠይቅ ያደርጉና ጉዳይዎ ሳይመረመር ስዊዘርላንድን ወድያው ለቀው መውጣት ኣለብዎት የሚል ውሳኔ ሊሆን የሚችልበት ምክንያቶች፡*

- *ባይሮፕላን ማረፊያ ማመልከቻ ከማቅረብዎ በፊት ባንድ የኤውሮጳ ማሕበር ኣባል ኣገር፣ በኣይስላንድ ወይም በኖርዌይ ውስጥ ከነበሩ፣ እርስዎ በምን መንገድ ወደ ስዊዘርላንድ እንደመጡ ኣጭር ቃለ መጠይቅ ያደርጋሉ። በቃለ መጠይቁም የርዳታ ድርጅት ኣባል ኣይካፈልም። እርስዎም ወደዚህ ኣገር ይመለሳሉ። የሚመለሱበት ኣገር የጥገኛነቱን ማመልከቻዎም ይሁን የርስዎን መባረር ያጣራል።*
- *ወደ ስዊዘርላንድ ከመምጣትዎ በፊት ወደ ሌላ ሶስተኛ ኣገር ለረጅም ጊዜ ከቆዩ ወይም ከኖሩ ወይም ደግሞ የርስዎን ዘመድ እዛ ይኖሩ ከሆነ።*
- *እርስዎ ወደ ሌላ፣ እርስዎን ከመመለስ ከለላ ወደሚሰጥ ኣገር መግባት የሚችሉ ከሆነ።*
- *በስዊዘርላንድ ወይም ሌላ የኤውሮጳ ኣገር ከዚህ ቀደም የጥገኝነት ማመልከቻ ኣቅርበው ከነበሩ እና ኣሁን ባቀረቡት የጥገኝነት ማመልከቻ ካዛው ለየት ያለ ኣዲስ የስደት ምክንያት ሳይገልጹ ከቀሩ።*
- *ወደ ስዊዘርላንድ የመጡት ጥገኝነት ለመጠየቅ ሳይሆን በሌላ ምክንያት የመጡ ከሆነ (በቤተሰብ ወይም ደግሞ በኤኮኖሚ ችግር ምክንያት)።*
- *ሃቀኛ የሆነ ማንነትዎ ከደበቁ (ስህተት ሰም፣ ስህተት የሆነ የትውልድ እለት ወዘተ)።*
- *ከስዊዘርላንድ መስርያ ቤቶች ማድረግ ያለብዎትን መተባበር ሳያደርጉ ሲቀሩ (ለምሳሌ ቃለ መጠይቅ የሚደረግበት ቀን ሳይገኙ ሲቀሩ)።*
- *የመታወቅያ ወረቀት ከሌልዎት ወይም በ48 ሰዓታት ውስጥ ለማውጣት የማይችሉ ከሆነ ወይም በቂ የሆነ ምክንያት ሳያቀርቡ ሲቀሩ እንዲሁም መስርያ ቤቱ ያቀረቡትን የስደት ምክንያት ፈጽሞ ስያምነው ሲቀር።*
- *በስዊዘርላንድ መስርያ ቤቶች ኣስተያየት የመጡበት ኣገር እንደ ዋስትና ያለው ኣገርና ከፖለቲካ ችግሮች ናጻ ነው ተብሎ የሚገመት ከሆነ እንዲሁም መስርያ ቤቱ ያቀረቡትን የስደት ምክንያት ፈጽሞ ሳያምነው ከቀረ።*
- *በስዊዘርላንድ ያለ ሕጋዊ ፍቓድ ይኖሩ ከነበረ እና እስር ቤት ከገቡ በኃላ የጥገኝነት ማመልከቻ ያቀረቡ ከሆነ እንዲሁም መስርያ ቤቱ ያቀረቡትን የስደት ምክንያት ፈጽሞ ሳያምነው ከቀር።*

***ማስትጠንቀቅያ፥ ይግባይ ብለው ኣበቱታ ካላቀረቡ ወይም ደግሞ ያቀረቡትን ኣቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀርና ኣሉታዊ ወሳኔ ከተሰጠው በስዊዘርላንድ ያለ ሕጋዊ መንገድ እንደሚኖሩ ነው የሚቆጠረው።***

***የኣሉታዊው ውሳኔ ምክንያት እንደተሰጠው እንዲሁም እንደ ኣይነቱ እስከ እስር ቤት መግባት ድረስ ሊሆን ይችላል።***

***ይግባኝ ካመለከቱ፣ እስኪወሰን ድረስ፣ በደንቡ መሰረት ስዊዘርላንድ ውስጥ መቆየት ይችላሉ።***

*እንዲያውቁት፤ ልዩ የሆነ ነገር ኣለ፡ ከዚህ በፊት ባንድ የኤውሮጳ ማሕበር ኣባል በሆነ ኣገር፣ በኣይስላንድ ወይም በኖርዌይ ውስጥ ከነበሩና ይህም ኣገር የርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ የመመርመር ሓላፊነት ያለው ከሆነ። እንደዚህ ቢሆንም ይግባኙ እስኪወሰን ድረስ ስዊዘርላንድ ውስጥ ሆነው ለመጠበቅ እንዲችሉ መጠየቅ ይችላሉ። ይሄንን ግን በተለይም የርስዎን ጉዳይ በሚመለከት ኣስፍተው ምክንያት ማቅረብ ኣለብዎት። ስዊዘርላንድ ውስጥ ለመቆየት ይጠይቁ፣ ምክንያት ካለዎት፣ የኤውሮጳው ኣገር ለምሳሌ እርስዎን፡*

- *በቀጥታ ወደ ግርፋት፣ ኢሰብኣዊ ወይም የሚያዋርድ ቅጣት ወይም ግፍ ወደሚደርስብዎ ትውልድ ኣገርዎ የሚልክዎት ከሆነ*
- *ለጥገኛነት ብቁ እያሉ፣ የጥገኛነት ማመልከቻዎን ሳይመረምር ወደ ትውልድ ኣገርዎ የሚመልስዎት ከሆነ።*

*ሓልፊነት ወዳለበት የኤውሮጳ ኣገር ቢላኩም እንኳን፣ የይግባኝ ማመልከቻዎ ስዊዘርላንድ ውስጥ ይወሰናል። ለፌደራል ኣስተዳደር ፍርድ ቤት*(Bundesverwaltungsgericht) *ዉሳኔው ወደ ውጭ ኣገር የት መላክ እንደሚላክ ይንገሩ። ጠበቃ ካለዎት፣ ውጭ ኣገርም ሆነው፣ ግንኙነት ኣያቋርጡ። እንደዛ ከሆነ ብቻ ነው እርስዎን ኣዎንታዊ ውሳኔ፣ ወደ ስዊዘርላንድ የመግባት ፈቃድ፣ ሊነገርዎት የሚቻለው።*




## 5 ይግባይ ማለት

**የውጭ ኣገር ስደተኖች ጉዳይ ኣጣሪ መስርያ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ያልተስማሙ ከሆነ በጽሁፍ መልክ ወደ ቀጥሎ የተጻፈውን ኣድራሻ ይግባይ ብለው ኣቤቱታ መላክ ይችላሉ።**

Bundesverwaltungsgericht
Postfach, CH-3000 Bern 14
**ተሌፎን** +41 (0)58 705 26 26
**ፋክስ** +41 (0)58 705 29 80

**ጉዳይዎ ባይሮፕላን ማረፊያ ሲጣራ፣ ይግባኝ ለማለት ኣምስት ቀናት ብቻ ነው ጊዜ ያለዎት።**

**የሕግ ማስረጃ የሚሰጡ መስርያ ቤቶች ወይም ደግሞ ጠበቃዎች ከርስዎ ጋር ሊተባበሩ ይችላሉ።** (**በዛው የኣድራሻዎች ዝርዝር ወይም ደግሞ በሚቀጥለው ዌብ ሳይት ተመልከት፡** http://www.for-refugees.ch) **የስዊዘርላንድ የስደተኞች ረዳት ድርጅት** (SFH) **በንዴት ኣኳሃን ይግባይ ማለት እንደምትችሉ የሚገልጽ ማስረጃ** Beschwerdeanleitung: http://www.fluechtlingshilfe.ch/hilfe/informationsblaetter **ኣዘጋጅቷል።**

**ኣይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ያሉ የሕግ ማማከሪያ ጽሕፈት ቤቶች ኣድራሻ**

Zürich-Kloten

SRK, Sozial-, Rechtsberatung, Transit ZH-Airport, Tel. 043 816 57 82, Fax 043 816 57 83

Genf-Cointrin
ELISA, Permanence Aéroport, Case postale 110, 1211 Genève 7, Tel. 022-733 82 62, Fax 022-733 82 47

**በካንቶኖች ላይ የሚገኙት ኣድራሻዎች ከፈለጉ እዚሁ ዌብ ሳይት ላይ ተመልከቱ፧**

http://www.fluechtlingshilfe.ch/hilfe/nuetzliche-adressen

# 6 ኣጠቃላይ ማስረጃ

**የሕግ ማስረጃ የሚሰጥ፣ ጠበቃ**
የሕግ እርዳታ ካስፈልግዎት በግል መፈለግ ኣለብዎት። የሕግ ማስረጃ የሚሰጥበት የእርዳታ ማህበር ቀጥሎ በተሰጠው ዌብ ሳይት ማግኘት ይቻላል www.for-refugees.ch/ ወይም ደግሞ ባንድ ሌላ የኣድራሻዎች ዝርዝር ያለበት ሰነድ ማግኘት ይችላሉ።

**ቤተሰብ እንዲመጡ የማድረግ፣ ከቤተሰብ ኣንድ ላይ መሆን**

ጥገኝነት ጠያቂዎች ቤተሰቦቻቸውን ካገር ቤት ለማስመጣት ፍቃድ የላቸውም።

**እርዳታ (ሶዝያል ሂልፈ)፣ ኣስቸኳይ እርዳታ**
እርዳታ የሚስፈልጋቸው የጥገኝነት ኣመልካቾች ሁሉ የጥገኝነት ጉዳያቸው በሚካሄድበት ጊዜ እርዳታ ይሰጣቸዋል።

በስዊዘርላንድ ሕገ መንግስት (ዓንቀጽ 12) መሰረት ሁሉ በስዊዘርላንድ የሚኖር ግለሰብ ችግር ሲያጋጥመው እርዳታ እንዲደረግለት ይደረጋል። ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ኣሉታዊ ውሳኔ ከተሰጠው ይሄን ኣገር ለቀው እስከሚውጡ ድረስ **እርዳታ የማግኘት መብት** ኣልዎት ይህ ማለትም ምንም እንኳ በስዊዘርላንድ **ያለ ሕጋዊ ፍቃድ** ቢኖሩ እርዳታ ይሰጥዎታል ማለት ነው። የሚደረገውም እርዳታ እንደ **ምግብ፣ የመኖርያ ቦታ፣ ልብስና፣ እንዲሁም በችግር ጊዜ የሚደረገውን የጤና ጥበቃ** ኣከታተል የሚያጠቃልል ነው። እንደዚህ ኣይነት እርዳታ ለማግኘት፣ እርስዎን እንዲወጡ ሓላፊነት ወዳለው ጽሕፈት ቤት፣ ማመልከቻ ማቅረብ ኣለብዎት፤ ግን ማመልክቻ ካቀረቡ እስርቤት የመግባት ያለው እድል ትልቅ ይሆናል። ተጨማሪ ማስረጃ እዚሁ ዌብ ሳይት ላይ ማግኘት ይችላሉ፥ www.for-refugees.ch/

**ስራ**
መስርያ ቤቶቹ የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ በኋላ በመጀመርያው ሶስት እስከ ስድስት ወር ያለው ጊዜ ስራ እንዲሰሩ ኣይፈቀድም። ካዛ በኋላ ግን ሰራ ለመስራት ይፈቀድልዎታል ነገር ግን በጥቂት የስራ ዓይነቶች ብቻ ነው መስራት የሚፈቀድልዎት እንዲሁም ስራ ለሚፈልጉ ያገሩ ተወላጆች ነው ቅድሚያ የሚሰጣቸው።

**የመኖርያ ቦታ**
ኣድራሻዎን በሚለውጡበት ጊዜ ለሚመለከታቸው መስርያ ቤቶች ወድያው ማስታወቅ ኣለብዎት። በኣጠቃላይ ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ የሚገኙ ሰዎች ካንድ ካንቶን ወደ ሌላ መለውጥ ኣይፈቀድላቸውም።

**እስር ቤት መግባት**
እስር ቤት ሊያስገብዎት የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፥
→ ያቀረቡት የጥገኝነት ማመልከቻ የማይታመን ነው ተብሎ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆን።
→ ከመስርያ ቤቶቹ ጋር ኣለመተባበር።
→ ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ሕገወጥ ሆኖ ሲገኝ።
→ ወንጀል ሰርተው ሲገኙ።
→ ወደ ኣገርዎ እንዳይመለሱ ለመቃወም የሚያደርጉትን ተቃውሞ የሚገልጽ ተጨባች ማስረጃ ከተገኘብዎት።

**ወደ ውጭ ኣገር መጓዝ**
የጥገኝነት ማመልከቻ በምታቀርቡበት ጊዜ ከስዊዘርላንድ ወጥተው ወደ ሌላ ኣገር ለመጓዝ ኣይፈቀድልዎትም። እንዲሁም ከኣገርዎ ቆንስል ጋር ወይም ሌላ ያገርዎ መስርያ ቤት ግንኙነት ማድረግ ኣይፈቀድልዎትም።